የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ለትብብር ምስረታ ብሎ የትግል ኣላማውን ለድርድር ኣያቀርብም!

(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)

በኦነግ የሚመራው የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ኣላማ ኣንድና ኣንድ ነው። እሱም የኦሮሞን ህዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ማረጋገጥ ነው። የወደፊቱን የኦሮምያና የኢትዮጵያ ሁኔታ በተመለከተ ከህዝቦች ጋር የፖለቲካ ኣንድነት የመፍጠር ወይም የራስን ነፃ መንግስት መስርቶ በጉርብትና የመኖር እድል የመወሰን መብት ያለው ባለጉዳዩ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ነው። የኦነግ ድርጅታዊ ሃላፊነት ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ይህንን የተከበረ መብቱን ለማረጋገጥ የሚችልበትን እድል ለማመቻቸት መታገል ይሆናል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ኣንዳንድ በኢትዮጵያ ኣንድነት ስም የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ኣላማችሁን ትታችሁ ወደኛ መስመር ተቀላቀሉ እያሉ በኦነግ ላይ ጫና ለማሳደር ይዳዳቸዋል። በተለይም ከነዚህ ሃይሎች ኣንዱ የሆነው ግንቦት 7 ከቀደሙት የኣማራ የፖለቲካ ልህቃን በተለየ መልኩ የኦሮሞ ህዝብ ትግል ኣላማ ፍትሃዊነት የገባው ቢያስመስልም የሚጠበቁበትን ተጨባጭ የኣመለካከት ለውጦችን ለማሳየት ግን ኣልደፈረም። እንዲያውም ይባስ ብሎ የኦሮሞን ህዝብ የነፃነት ትግል ጎራ ከፋፍሎ ለማዳከም በግልፅም ሆነ በስውር ጥረቶችን ወደ ማድረግ ከገባ ቆይቷል። ያገኘውን ቀዳዳ ሁሉ በመጠቀም ይህንን እኩይ ጥረቱን ፍሬያማ ለማድረግ ተንቀሳቅሷል፣ ኣሁንም በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ከፍተኛ የኣመራር ኣባላቱ ሳይቀር በዚህ ጥረት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ ታዝበናቸዋል። በኦሮሞ ህዝብ ትግል ጎራ ውስጥ ወንጀል በመፈፀማቸው ተቀባይነትን ያጡ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ግለሰቦችን የኣላማቸው መጠቀሚያ ለማድረግም መልምለዋል።

እነ ግንቦት 7 ይህን በማድረጋቸው የኦሮሞ ህዝብ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ዛሬ በኣንድ ድምፅ እያሰማ ያለው ቁጣ በገሃድ የሚታወቅ ነው። ይህ የህዝቡን ትግል ኣይደፈሬነት የሚያረጋግጥ ቁጣ ዳግማዊ ወያኔና ዳግማዊ ኦፒዲኦ ለመሆን ለተጫጨት ወገኖች በቂ ትምህርት ይሰጣል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል። እነ ግንቦት 7 ያለ ኦሮሞ ህዝብ ተሳትፎና እሺታ ትግላቸው ሊሰምር እንደማይችል ለማመን መገደዳቸው ኣያስገርምም። ዋናው ኣስፈላጊ ነገር የዚህን ብዙሃን ህዝብ ፍላጎት ኣምኖ መቀበልና ጊዜ ካለፈበት የብልጣብልጥነት ፖለቲካ መቆጠብ ነበር። ያን በማድረግ ፋንታ የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ ስልት ኮርጆ የኦሮሞን ትግል ለማዳከም ማለም ትርፉ ውድቀት ብቻ ይሆናል።

ግንቦት 7 ለሁሉም የሚበጅ የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት ቆርጦ የተነሳ ቢሆን ኖሮ ወሳኝ ድምፅ ያለውን የኦሮሞ ህዝብ ውሳኔ ባልፈራ ነበር። ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የኦሮሞን ህዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እቀበላለሁ ብሎ ኣፉን ሞልቶ መናገር ነበረበት። በተቃራኒው ግን ንቅናቄው የሚያራምደው ኣላማ የኦሮምያን ስምና ካርታ ፍቆ የኣባቶቹን ኣሃዳዊ ስርኣት መልሶ መዘርጋትን

ነው። የኦሮሞን ህዝብ የብሄረተኛነት ስሜት በመሸርሸር በእያንዳንዱ የኦሮሞ ዜጋ ልብ ውስጥ የተሸናፊነት ስነ ልቦና እንዲሰርፅና ኢትዮጵያዊነትን መቀበል ብቸኛው የህዝቡ እጣ ፈንታ ተደርጎ እንዲታመን መወትወትን ነው። ኣልሸሹም ዞር ኣሉ ነው ነገሩ።

እንዲህ ላለው ከንቱ መንጫጫት የኦሮሞ ህዝብ ጆሮ የለውም። እነ ግንቦት 7 ኣልተረዱትም ኣልያም እየተረዱት ኣምነው መቀበሉ እንደ እሬት መሮኣቸው ይሆናል እንጂ ዛሬ የኦሮሞ ህዝብ የብሄረተኛነት ደረጃ ከቶ ሊቀለበስ በማይችል መልኩ እጅግ ብዙ ማይሎችን ርቆ ወደፊት ገስግሷል። ተወደደም ተጠላም ዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጣ የሚወሰነው በብዙሃኑ የኦሮሞ ህዝብና እንደሱ ባሉት የተጨቆኑ ህዝቦች እንጂ ሃፍረት በማይሰማቸው ጥቂት ብልጣብልጥ ነን ባይ ፖለቲከኞች ኣይደለም።

ይህ ሃቅ የሚመር ቢሆንም ኣምኖ ከመቀበል ሌላ ኣዋጭ ኣማራጭ ኣይኖርም። ይህን ኣምኖ መቀበል ደግሞ በቅድሚያ የኦሮሞን ህዝብ ታላቅነት ከዚያም ኦነግ የዚህ ታላቅ ህዝብ መሪ ድርጅት መሆኑን ያለማመንታት መቀበልን ይጠይቃል። ታላቁ የኦሮሞ ህዝብ በጣት በሚቆጠሩ ወንጀለኛ ግለሰቦች ሴራ የማይከፋፈልና ኣንድ ፅኑ የጋራ ኣላማ እንዳለው መገንዘቡም ጠቃሚ ይሆናል። ይህ ግንዛቤ ከተገኘ በሁዋላ የራስህን ኣላማ ትተህ የኔን ኣላማ ተቀበል የሚለው ያረጀ ያፈጀው የትምክህተኛነት ኣመለካከት ዛሬ ጨርሶ ቦታ እንደማይኖረው መረዳቱ የሚቸግር ኣይሆንም። ይህን ኣስፈላጊ ግንዛቤ መጨበጥ ለባሰ መዘዝ የሚያጋልጡ የብልጣብልጥነት እግሮችን ኣስቀድሞ በመሰብሰብ ኣደገኛ የፖለቲካ ፈንጅ ከመርገጥም ያድናል።

በትክክል መታወቅ ያለበት ጉዳይ ኦነግ ከሌሎች ጋር የትግል ትብብር ለመፍጠር ብሎ የራሱን የፖለቲካ ኣላማ ለድርድር ኣያቀርብም። የፖለቲካ ኣላማህን ቀይረህ የኔን ካልተቀበልክ በስተቀር ካንተ ጋር ኣልተባበርም የሚሉ ካሉ የሚያዋጣቸውን ሌላ መንገድ መፈተሽ መብታቸው ነው። እንዲህ ካሉት ሃይሎች ጋር የሚፈጠር የትግል ትብብርም ወንዝ የሚያሻግር ትብብር ሊሆን ኣይችልም። እንደዚህ የሚያስቡ ሃይሎች የኦሮሞን ህዝብ የብዙሃንነት ድምፅ ስለሚፈሩ ከተቻለላቸው በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ እኛቸውን ኣስገብተው የታጋዮቹን ኣንድነት ለማላላት ከመጣር ኣይቆጠቡም። ግንቦት 7ም በኦሮሞ ህዝብ የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ እጁን ከማስገባት እንዲቆጠብና ፊቱን ወደ ጋራ ጠላታችን እንዲመልስ ኣበክረን እናሳስባለን።

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ